# ጠምና ትርጉሙ

ከብሂል ጎላ ያለ ትምህርት እናገኛለንና እስኪ ስለጠም የተዛባ መረዳት እንዳለን የሚጠቁም ብሂል ላጫውታችሁ።

ነገሩ እንዲህ ነው ሰውዬው ገጠር የሚኖርና፤ ባለትዳር ነው። ብዙ ጊዜ በገጠር ሰው ከሰው የሚጣላው  በመሬት ነው፤ ድንበር ገፋኸኝ፤ ገፋኸኝ በመባባል። እንግዲህ የአገራችን የኑሮ መሠረቱ እርሻ እንደመሆኑ በመሬት የመጣ ነገር ገበሬው አይሆንለትም። ከዕለታት አንድ ቀን ከድንበርተኛው ጋር  ይጣላና ሊደባደብ ፈልጎ ባጋጣሚ በእጁ ዱላ አልነበረም።ቤቱ አቅራቢያ ስለነበር ሄድ ብሎ ባለቤቱን ያ ዱላዬ የት ሄደ አቀብይኝ የት አለ? ይላታል፤ ባለቤቱም ምነው ያለድሮህ በዚህ ሰዓት መጣህ? በደህና ነው? ምሳ አዘጋጅቼ ልመጣ ጉድ ጉድ ስል ነበር።ታዲያ ቁጭ በልና እህል ቅመስ፣ ደግሞስ ዱላውን አሁን ለምን ፈለግኸው? የት እንዳለም እንጃ ትለዋለች፤አይ ወዲያ ይኸ ጥጋበኛ መሬቴን እየገፋኝ ስላስቸገረኝ ልኩን ላሳየው ነው።ቶሎ ዱላውን ፈልጊና አቀብይኝ፤ አንች ደግሞ ቀኑን ረሳሽው? ዓርብ እኮ ነው ገና ሰዓት ሳይደርስ ብላ ትይኛለሽ? ብሏት እርፍ።

ጠምን የምንረዳው እንዲህ ይሆን?

ደምለው ይነሱ

ኦስሎ